


# ትምህርት ከመጀመሩ በፊት

በ Waterloo Region ያሉ ውስብስብ ፍላጎት ያላቸውን ታዳጊ ሕፃናትን የሚደግፉ ኤጀንሲዎች ሕፃናትን እና ቤተሰቦችን ወደ ትምህርት ቤት እንዲሸጋገሩ ለመርዳት ከትምህርት ቤት ቦርዶች ጋር በጋራ ይሠራሉ። ሁሉም ቤተሰቦች የሚያስፈልጋቸውን መረጃ ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ ለሁሉም የሚያገለግል አንድ ሂደት አለ። ቤተሰቦችን ለመርዳት መሪነቱን የሚወስድ አንድ ሰው አለ፤ ይህም the Referral Source ተብሎ ይጠራል።

ሕጻኑ የሚከታተለው ፍቃድ የተሰጠው የሕፃናት እንክብካቤ አገልግሎትን ከሆነ the Referral Source የሚሆነው the Resource Consultant ነው። ሕፃኑ በሕፃናት እንክብካቤ ሥር ካልሆነ፣ the Referral Source የሚሆነው Family Infant Child Consultant፣ የ Ontario Autism Program ሠራተኛ፣ ወይም KidsAbility ቴራፒስት ነው።

ይህ በሽግግር ሂደቱ ውስጥ የሚከሰቱ ሦስት መሠረታዊ ነገሮች ዝርዝር ነው፡-

1. The Referral Source ልጅዎ የሚገባበት የትምህርት ቤት ቦርድ ውስጥ ደኅንነቱ ተጠብቆ በኤሌክትሮኒክ መንገድ የሚጋራ የኤሌክትሮኒክ መረጃ የማጋራት ፈቃድ ቅጽ እንዲፈርሙ ይጠይቅዎታል። ይህ የሚደረገው ከትምህርት መጀመሪያ ዓመቱ በፊት እስካለው የኖቬምበር ወር ድረስ ቀደም ብሎ ሊሆን ይችላል።
2. School Board Consultant ሪፖርቶችን በመጠቀም እና ፍቃድዎን የሰጧቸውን ኤጀንሲዎች በማነጋገር ስለ ልጅዎ መረጃ ያሰባስባል።
3. አስፈላጊ ከሆነ መረጃ ለማጋራት እና በሴፕቴምበር ወር ላይ ጥሩ የሆነ አጀማመር እንዲኖር ለማቀድ የ Transition to School ስብሰባ ሊደረግ ይችላል። የሽግግር ስብሰባዎች በአብዛኛው በጸደይ እንዲሁም አንዳንዴ በበልግ ወቅት መጀመሪያ ላይ በስልክ፣ በቪዲዮ ኮንፍረንስ፣ ወይም በአካል ሊደረጉ ይችላሉ።

## <u>ትምህርት ቤት ለመግባት ማቀድ</u>

**የመረጃ ፈቃድ ቅጽ፡-** The Referral Source መሠረታዊ መረጃዎችን ደኅንነቱ በተጠበቀ፣ በኤሌክትሮኒክ መንገድ፣ እንዲሁም ከልጅዎ ጋር በተያያዙ የማኅበረሰብ ኤጀንሲዎች መካከል በቃል የተሰጠን መረጃ በስልክ እንዲሁም በጽሑፍ የቀረቡ ሪፖርቶችን ለትምህርት ቤቱ ቦርድ ለማጋራት የወላጅን/ሕጋዊ አሳዳጊን ፈቃድ ይጠይቃል። ይህም መረጃ የሚከተሉትን ያካትታል፡- የልጅዎን ስም፣ አድራሻ፣ የልጅዎን የሕዝብ ትምህርት ቤት፣ ልጅዎ የሚያገኛቸውን አገልግሎቶች እና ቅጹ ለማን እንደሚላክ የሚገልጽ መረጃ። እርስዎ ፈቃድዎን ከሰጡ በኋላ የልጅዎ የግምገማ ሪፖርት፣ የድጋፍ ዕቅድ፣ ጥንካሬዎች፣ እና ፍላጎቶች ይጋራሉ። የመረጃ ፈቃድ ቅጹ ልጅዎ ለተመዘገበበት የትምህርት ቤት ቦርድ የሚጋራ ይሆናል። እባክዎን ያስተውሉ፡- ለትምህርት ቤቱ ቦርድ የሚጋሩ ቅጾች ለትምህርት ቤቱ ሠራተኞች፣ ለልዩ ፍላጎት ትምህርት ሠራተኞች ወይም ሌሎች ተገቢ የተምህርት ቤቱ ሠራተኞች ሊጋሩ ይችላሉ። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ለበለጠ መረጃ እና ፈቃድ ሌሎች የትምህርት ቤቱ ሠራተኞች ሊያነጋግሩዎት ይችላሉ።

**የቴራፒ አገልግሎቶች በትምህርት ቤት ሥርዓት ውስጥ ፡-** ከ KidsAbility አገልግሎት ለሚያገኙ ልጆች፣ የቴራፒ ሠራተኞች ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር በመሆን የሪፈራል ሂደቱን እና የቴራፒ ሂደቱ አሁን እየተሰጠበት ካለው እንዴት እንደሚለያይ ይገመግማሉ።

**መረጃ ማሰባሰብ ፡-** School Board Consultants *ሪፖርቶችን እና የሪፈራል ምንጮችን ጨምሮ ከተለያዩ ምንጮች መረጃን ሊሰበስቡ ይችላሉ። የትምህርት ቤቶች ቤተሰብ አካል በመሆናቸው በመዋዕለ ሕፃናት የግንዛቤ ማስጨበጫ ዝግጅቶች ላይ ሊያናግሩዎት ይችላሉ። በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ ልጅዎ የሕዝብ ትምህርት ቤት ውስጥ እንዲማር ማሻሻያዎች ካስፈለጉ* the School Board Consultant *ልጅዎን በፕሮግራሙ ውስጥ ሊከታተል ይችላል። ከዚያም* School Board Consultants *አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለማጋራት ልጅዎ የሚማርበትን ትምህርት ቤት ርዕሰ-መምህር ያነጋገራሉ።*

**ምዝገባ ፡- ወላጆች/አሳዳጊዎች ልጃቸውን መዋዕለ ሕፃናት ያስመዘግባሉ።** *የምዝገባ መረጃ ለማግኘት የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ጋር ይደውሉ፣* the Waterloo Region District School Board *ድሕረ-ገጽን ይጎብኙ)* www.wrdsb.ca *ወይም* the Waterloo Catholic District School Board *ድሕረ-ገጽን ይጎብኙ*www.wcdsb.ca (*የሕዝብ ትምህርት ቤቱን አቅጣጫ ለማግኘት* ይህን ይጫኑ )።

*የልጅዎን የልደት ምስክር ወረቀት፣ የክትባት ወረቀት ወይም ከክፍያ ነጻ የመሆን ደብዳቤ ከ* the Waterloo Region Health Department*፣ የአድራሻ ማረጋገጫ እና ተዛማጅ የ* Catholic Baptismal Certificate *ለ* WCDSB *መውሰድ አለብዎት።*

*ልጆቻቸው* KidsAbility School *እንዲሁም የሕዝብ ትምህርት ቤት ለሚማሩ ወላጆች፣ ወላጅ/አሳዳጊዎች እያንዳንዱን ፕሮግራም ማነጋገር እና ልጃቸው ሁለቱንም ፕሮግራሞች እንደሚከታተል ማሳወቅ አለባቸው።*

**Transition to School ስብሰባዎች** ፡- Transition to School *ስብሰባ መታቀዱን በሚመለከት ወላጆች/አሳዳጊዎች መልእክት ሊደርሳቸው ይችላል። ስብሰባዎች በስልክ ወይም በቪዲዮ ኮንፈረንስ፣ ወይም በአካል ሊደረጉ ይችላሉ። እነዚህም የሚመቻቹት* the Referral Source *በሆነው በ* the Meeting Coordinator *ነው። ልዩ ሁኔታ፡- KidsAbility* the *Referral Source በሚሆንበት ጊዜ School Personnel* the *Meeting Coordinator ይሆናል።* ስብሰባ ከተዘጋጀ የልጅዎን ጥንካሬዎች እና ፍላጎቶች የተመለከተ መረጃ ለትምህርት ቤት ቡድኑ ይጋራል። (Tips for Parentsን ይመልከቱ)

*ለአንዳንድ ልጆች የ* Transition to School *ስብሰባ አስፈላጊ እንዳልሆነ በ* the School Consultant*፣* Referral Source*፣ እና በወላጅ/አሳዳጊ ሊወሰን ይችላል። በጋራ በመሆን መጋራት ያለበት መረጃ ምን እንደሆነ እና እንዴት እንደሚጋራ ትወስናላችሁ።*

*አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የ* Transition to School *ስብሰባ ወላጅ/አሳዳጊዎች፣ የትምህርት ቤት ሠራተኞች፣ የትምህርት ቤት የቦርድ ሠራተኞች፣ እና አሁን ላይ አገልግሎቱን የሚያቀርቡ የማኅበረሰብ አቅራቢዎችን ሊያሳትፍ ይችላል። እባክዎን ያስታውሱ፡- KidsAbility ቴራፒስቶች ብዙ ጊዜ በእነዚህ ስብሰባዎች ላይ አይገኙም።*

*ወላጅ/አሳዳጊዎች የትምህርት ቤት ጉብኝት እንዲዘጋጅ ሊጠይቁ ይችላሉ።*

## የTransition to School ስብሰባ መረጃ

**ይህ ስብሰባ የሚካሄደው መቼ ነው?**

· አስፈላጊ ከሆነ ልጅዎ በሴፕቴምበር ወር ትምህርት ከመጀመሩ በፊት በጸደይ ወይም በበልግ ወቅት ላይ የ Transition to School ስብሰባ ሊደረግ ይችላል።
· በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ የልጅዎ Referral Source የ Resource Consultant፣ Autism Program ሠራተኛ፣ ወይም Family Infant Child Consultant ከሆነ ወላጅ/አሳዳጊ እና የትምህርት ቤት ሠራተኞች የሚሳተፉበትን ቀን እና ሰዓት ያመቻቻል።
· ስብሰባው ከ 45- 60 ደቂቃዎች አካባቢ ሊቆይ ይችላል።

**የዚህ ስብሰባ ዓላማ ምንድነው?**

· ትምህርት ቤትዎ እንኳን ደኅና መጡ ሊልዎት እና ልጅዎ በትምህርት ቤቱ ውስጥ በአግባቡ እንደሚደገፍ ሊያረጋግጥልዎ ይፈልጋል።
· በስብሰባው ላይ የሚሳተፉ አካላት ሁሉ ስለ ልጅዎ ጥንካሬዎች፣ ፍላጎቶች እና ዝንባሌዎች መረጃ ከልጅዎ ትምህርት ቤት ጋር ይጋራሉ።
· ልጅዎ በትምህርት ቤት ጥሩ እና የተሳካ አጀማመር እንዲኖረው የሚረዱትን መንገዶች የሚለይ የትብብር ዕቅድ ይጀመራል።

**በዚህ ስብሰባ ላይ እነማን ይሳተፋሉ?**

· እርስዎ በስብሰባው ይሳተፋሉ። (እባክዎ ወደ ስብሰባው ማንን መጋበዝ እንደሚችሉ ከ Meeting Coordinator ጋር ይነጋገሩ)።
· የሕፃናት እንክብካቤ አገልግሎት አቅራቢዎ፣ Resource Consultant፣ Family Infant Child Consultant፣ ወይም የ Autism Program ሠራተኛ፣ እና ልጅዎን በመዋዕለ ሕፃናት ውስጥ የሚደግፈው the School Board ሠራተኛ ስብሰባውን ሊሳተፉ ይችላሉ።
· **እባክዎ ያስተውሉ፡-** KidsAbility Physiotherapists፣ Occupational Therapists፣ Speech-Language Pathologists፣ እና Social Workers የተለዩ ወይም ውስብስብ ሁኔታዎች ከሌሉ በስተቀር እነዚህን ስብሰባዎች አያዘጋጁም እንዲሁም አይሳተፉም።
· የቤተሰብ አባል ወይም ጓደኛ የሆነ ደጋፊ ሰው ወደ ስብሰባው ይዘው መሄድ ይችላሉ።
· ልጅዎን ወደ ስብሰባ ይዘው አይምጡ። ልጅዎ የትምህርት ቤቱን ሰዎች ስለሚያገኝበት ሌሎች አጋጣሚዎች መጠየቅ ይችላሉ።
· በአብዛኛው መምህራን ጥቂት ቆይተው ስለሆነ ወደሚያስተምሩበት ክፍል የሚመደቡት የልጅዎ የመዋዕለ ሕፃናት መምህር በዚህ ስብሰባ ላይሳተፍ ይችላል። ሌሎች የትምህርት ቤቱ ሰዎች በስብሰባው ላይ የሚሳተፉ ሲሆን ስለ ልጅዎ ያገኙትን መረጃ በሌላ ጊዜ ለመምህሩ የማካፈል እድል ይኖራቸዋል።

**ለስብሰባው እንዴት መዘጋጀት ይችላሉ?**

· ከልጅዎ ጋር አሁን እየሠሩ ያሉ ሰዎችን ያነጋግሩ። ሊረዱዎት ይችላሉ! ስለ ልጅዎ ለሁሉም ሰዎች በስብሰባው ላይ ለመናገር እድሉ ይኖርዎታል። ሁሉም ሰው የመናገር እድል ሊሰጠው ስለሚገባ ለመናገር ረጅም ሰዓት ላያገኙ ይችላሉ፤ ነገር ግን እርስዎ የሚሰጡት ሐሳብ የስብሰባው ጠቃሚ ክፍል ይሆናል።
· ልጅዎን ለሁሉም ሰው ለማስተዋወቅ የሚረዳዎትን አንድ ነገር ይዘው መሄድ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ ለሁሉም ሰው የልጅዎን ፎቶግራፍ ወይም 'All About Me' ጥቅል ማሳየት ይችላሉ።
· ትምህርት ቤቱ እንዲሰማቸው የሚፈልጉትን ዋና ነጥቦች አዘጋጅተው እንዳይረሱ በጽሑፍ ያስቀምጧቸው እና የጻፉትን ይዘው ወደ ስብሰባው መሄድ ይችላሉ።

· የቤተሰብ አባል ወይም ጓደኛ ካለዎት በስብሰባው ወቅት በእርስዎ ቦታ ማስታወሻዎችን እንዲይዝልዎት መጠየቅ ይችላሉ።

**በስብሰባው ወቅት ምን ይከሰታል?**

· The Meeting Coordinator ወይም School Principal በአብዛኛው ስብሰባውን የሚመሩ ሲሆን ቃለ-ጉባዔ መያዙን እና ከስብሰባው በኋላ ለሁሉም ሰው መላኩን ያረጋግጣሉ።

· እርስዎንም ጨምሮ ሁሉም ልጅዎን የሚያውቁ ተሳታፊዎች ስለ ልጅዎ ለመናገር አጠር ያለ ጊዜ ይሰጣችኋል።

· ከትምህርት ቤቱ የመጡ ተሳታፊዎች እናንተ የምትናገሩትን በማዳመጥ ልጅዎን የበለጠ መረዳት እንዲችሉ ጥያቄዎችን ሊጠይቁ ይችላሉ። በተቻለዎት መጠን ስለ ልጅዎ ፍላጎቶች በጣም በግልጽነት ይናገሩ፤ ምክንያቱም ይህ ትምህርት ቤቱ ልጅዎን ለመደገፍ በተሻለ ሁኔታ እንዲዘጋጅ ያግዘዋል።

· በዚህ ስብሰባ ላይ የሚታቀዱ አንዳንድ ቀጣይ እርምጃዎች ይኖራሉ፤ ነገር ግን ብዙ ዝርዝሮች እና የመጨረሻ ዕቅዶች በዚህ ስብሰባ ላይ አይወሰኑም።

· እንደ ሪፈራል ቅጾች እና የፈቃድ ቅጾች የመሳሰሉ አንዳንድ ቅጾችን እንዲፈርሙ ሊጠየቁ ይችላሉ።

· ስለማናቸውም ሐሳቦች፣ ጥያቄዎች፣ ወይም ዕቅዶች እርግጠኛ ካልሆኑ ጥያቄዎችን ይጠይቁ እንዲሁም ለማሰብ ለራስዎ ጊዜ ይስጡ።

· በቀጣዮቹ ጥቂት ወራት ማናቸውም ጥያቄዎች ካሉዎት ማንን ማነጋገር እንደሚችሉ ይጠይቁ።

**በ 'All About Me' ቡክሌት ውስጥ ምን ማካተት አለብኝ?**

መረጃው የሚከተለውን ሊያካትት ይችላል፡-

- · የልጅዎን ፎቶግራፍ
- · ቤተሰብን፣ እህት እና ወንድሞችን፣ የቤት ውስጥ ለማዳ እንስሳትን የተመለከተ መረጃ
- · ከልጅዎ እይታ አንጻር ያሉ ቃላት
- · ልጅዎን ለመግለጽ ሰዎች የሚጠቀሙበት ቃላት (ለምሳሌ፡- ደስተኛ፣ አስቂኝ፣ ትዕዛዛዎ፣ ስሜታዊ)
- · ልጅዎ በጣም ጥሩ የሆነባቸው ነገሮች (ለምሳሌ፡- የሚወዳቸው ነገሮች፣ ልዩ ዝንባሌዎች)
- · የሚገጥሙ ተግዳሮቶች (ለምሳሌ፡- የሚያስጨንቁት ወይም የሚያበሳጩት ነገሮች)
- · ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ ስልቶች (ለምሳሌ፡- ስለ ሽግግር ሊያሳውቁት የሚችሉ ምስሎች፣ ተረጋግቶ እንዲቆይ የሚያደርጉት ቁልፍ ቃላት)
- · እናንተ ማወቅ ያለባችሁ ነገሮች (ለምሳሌ፡- አለርጂዎች፣ የምግብ ስጋቶች፣ መድኃኒቶች)
- · በዚህ ዓመት እርስዎ እና ልጅዎ የምትጓጉለት ነገር

**ትምህርት ቤቱን መቼ መጎብኘት እችላለሁ?**

- · በጁን ወር ላይ ወይም በኦገስት የመጨረሻ ሳምንት ላይ ትምህርት ቤቱን ለመጎብኘት ለመጠየቅ the Principal ወይም የትምህርት ቤቱን Secretary ያነጋግሩ።
- · ቅዳሜ እና እሁድ ላይ ወይም ከትምህርት ሰዓት በኋላ ከልጅዎ ጋር በመሆን የትምህርት ቤቱን የጨዋታ ሜዳ በመጎብኘት አዲሱ ትምህርት ቤት ውስጥ ምን መጠበቅ እንዳለበት ከልጅዎ ጋር ተነጋገሩ።

<u>ምሕጻረ-ቃላት እኛ ፍቺያቸው</u>

| ስም | ምሕጻረ-ቃል | ፍቺ |
|---|---|---|
| Home and Community Care Support Services-Waterloo Wellington (የቤት እና የማኅበረሰብ እንክብካቤ ድጋፍ አገልግሎቶች - Waterloo Wellington) | **HCCSS** | እነዚህ ባለሙያዎች የጤና እና የቴራፒ ፍላጎቶችዎን በተመለከተ ግምገማ እና ምክር ይሰጣሉ |
| Home and Community Care Support Services - School Health Support Services (የቤት እና የማኅበረሰብ እንክብካቤ ድጋፍ አገልግሎቶች - የትምህርት ቤት የጤና ድጋፍ አገልግሎቶች) | **HCCSS-SHSS** | Home and Community Care Support Services - School Health Support Services |
| Full-Day Kindergarten (የሙሉ ቀን መዋዕለ  ሕፃናት) | **FDK** | ልጅን ማዕከል ያደረገ፣ ለእድገት ተስማሚ፣ የተቀናጀ፣ ለዐራት እና አምስት ዓመት ሕፃናት የተራዘመ የትምህርት ቀን ነው። |
| Individual Educational Plan (የግለሰብ የትምህርት ዕቅድ) | **IEP** | ልጆች በትምህርት ቤት ስኬታማ እንዲሆኑ ለመርዳት የተጻፈ IEP በመምህራን እና ወላጆች ይዘጋጃል። |
| Identification, Placement and Review Committee (የመለያ፣ ምደባ እና የግምገማ ኮሚቴ) | **IPRC** | ይህ ኮሚቴ አንድ ልጅ በተግባቦት፣ በአእምሮ፣ በአካል፣ በሥነ-ባሕርይ፣ በተለያዩ ጉዳዮች ልዩ ተብሎ የሚመደብ መሆን አለመሆኑን እንዲሁም በደንብ ተገቢ የሆነው ምደባ የቱ እንደሆነ ይለያል። |
| Ontario Education Number (Ontario የትምህርት ቁጥር) | **OEN** | ይህ ለልጅዎ በ Ministry of Education (ትምህርት ሚኒስቴር) የተሰጠ እና እስከ አንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ድረስ የሚያገለግል የመለያ ቁጥር ነው። |
| Ontario Student Record (Ontario የተማሪ መዝገብ) | **OSR** | OSR በትምህርት ዓመታቱ ውስጥ የልጅዎ የትምህርት እድገት ሂደት የሚመዘገብበት ምስጢራዊ መዝገብ ነው። ወላጆች፣ ርዕሰ-መምህራን እና መምህራን OSR ማግኘት እና መመልከት ይችላሉ። |
| Special Education | **SEAC** | ይህ ኮሚቴ ስለ ልዩ ፍላጎት ትምህርት |

| | | |
|---|---|---|
| Advisory Committee (የልዩ ፍላጎት ትምህርት አማካሪ ኮሚቴ) | | ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች ባለ አደራዎችን እና የትምህርት ቤት ቦርድ አስተዳደርን ያማክራል። |
| Special Education Resource Teacher (የልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህር) | **SERT** | ይህ መምህር በልዩ ፍላጎት ትምህርት ተጨማሪ የትምህርት ዝግጅት ያለው ሲሆን ከክፍል መምህሩ ጋር በመሆን የልጅዎን ፍላጎቶች ለማሟላት ይሠራል። |
| Special Equipment Amount (የልዩ ፍላጎት መሣሪያ ገንዘብ) | **SEA** | SEA የገንዘብ ድጋፍ ብቃት ባለው ባለሙያ ለተማሪው የትምህርት ቤት ስኬት አስፈላጊ የሆነ መሣሪያ እንዲገዛ ሐሳብ ሲቀርብ ያንን መሣሪያ ለመግዛት የሚውል ገንዘብ ነው። |
| Transition to School (ወደ ትምህርት ቤት ሽግግር) | **TTS** | ይህም ሁሉም ልጆች በተሳካ ሁኔታ ወደ አዲሱ ትምህርት ቤታቸው እንዲገቡ ለመርዳት መረጃ የማካፈል እና የመዘጋጀት ሂደት ነው። |
| Waterloo Catholic District School Board (Waterloo የካቶሊክ ዲስትሪክት ትምህርት ቤት ቦርድ) | **WCDSB** | WCDSB በ Chatholic Schools ውስጥ ያሉ የተለያዩ የተማሪዎችን ፍላጎቶች ለማሟላት ፕሮግራሞችን እና አገልግሎቶችን የሚያቀርብ ነው። |
| Waterloo Region District School Board (Waterloo Region ዲስትሪክት የትምህርት ቤት ቦርድ) | **WRDSB** | የ WRDSB የልዩ ፍላጎት የትምህርት ፕሮግራም ሁሉም ተማሪ ማግኘት በሚቻለው በከፍተኛ ሁኔታ ጠቃሚ በሆነ የትምህርት ከባቢ ውስጥ የመማር መብት አለው በሚል ፍልስፍና ላይ የተመሠረተ ነው። |

ማስታወሻ:-

የልጅዎን ወደ ትምህርት ቤት የመሸጋገሪያ ወቅት ለመደገፍ በጋራ መሥራት!